መብ
ትህን
እወቅ

# ACLU Nevada

## በኔቫዳ የተቃዋሚዎች መብት

የመናገር እና የመሰብሰብ ነፃነትዎን መጠቀም፣ በመጀመሪያው ማሻሻያ (First Amendment) ሥር በግልጽ የተጠበቀ ነው። ይሁን እንጂ፣ የጅምላ ሰልፎች ከፖሊስ ጋር ያልተፈለገ ግንኙነት፣ እስር — አለፍ ሲልም የሃይል አመጽ ልያስከትል ይችላል። ተቃውሞ ለማሰማት እየሄዱ ከሆነ፣ መብቶችዎ ለማወቅ የምያስፈልግዎ ነገር እዚህ አሉ።

### መቃወም የምችለው የት ነው?

በአካል ተገኝቶ ተቃውሞዎች ማሰማት ብቸኛው ዓይነት ተቃውሞ አይደሉም፤ ሆኖም፣ የተለመዱ እና በአካል ተሰባስቦ መንግስትን መቃወም ጥንታዊው የአመሪካውያን ባህል ነው።

በአካል ተገኝቶ ተቃውሞ ማሰማት በጐዳና፣ በእግረኛ መንገድ፣ በአደባባይ ወይም በመናፈሻ ባሉ የሕዝብ ንብረት ላይ ሊካሄዱ ይችላሉ። እነዚህ አካባቢዎች ባህላዊ የህዝብ መድረኮች በመባል የሚጠሩ ሲሆን፣ ከፍተኛውን የ 1A ጥበቃዎች ይሰጣሉ።

በአካል ተገኝቶ የሚደረጉ ተቃውሞዎች፣ በመንግሥት ሕንጻዎች ውስጥም ሊካሄዱ ይችላሉ። መንግሥት እነዚህን ተቃውሞዎች የሚገድቡ ተጨማሪ ደንቦችን ማውጣት ይችላል፤ ነገር ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ መሆን አለባቸው። መንግሥትም አንድን የተቃውሞ ቡድን በልዩ ደንቦች ወይም ገደቦች ዒላማ ማድረግ አይችልም።

አንዳንድ የተቃውሞ ሰልፎች ፈቃድ ልያስፈልጋቸው ይችላል፤ ነገር ግን፣ የተቃውሞ ሰልፉ ከመንገድ ዳርቻዎች/ከጎዳና ማገጃዎች የሚወጣ ከሆነ፣ ከፍተኛ ድምፅ የሚጠቀም ትልቅ ሰልፍ ከሆነ ወይም ከሕዝባዊ መናፈሻዎች ወይም የፍርድ ቤቶች የመጠን ገደቦች የሚያልፍ ከሆነ ብቻ ነው። በተቃውሞው ይዘት ምክንያት መንግሥት ፈቃድ መስጠትም ሆነ መከልከል አይችልም።

የመጀመርያው የማሻሻያ መብቶችዎ በመኖሪያ ሰፈሮች ውስጥ ይበልጥ የተገደቡ ናቸው። አንድን መኖሪያ ዒላማ ማድረግ፣ እንደ የረብሻ ድንጋጌዎች ያሉ ሕገ መንግሥታዊ ተቀባይነት ያላቸውን ሕጎች ሊጥስ ይችላል።

የግል ንብረት ባለቤቶች በንብረታቸው ላይ የንግግር፣ የፎቶግራፍ ወይም የቪዲዮ ቀረጻ ደንቦችን ሊያወጡ ይችላሉ፤ ይህም፣ የግል ንብረት ተጠቅሞ መቃወም አስቸጋሪ ያደርገዋል።



### ሕጋዊ የሆኑ የተቃውሞ ዘዴዎች የትኞች ናቸው?

ተቃውሞን ሕገ ወጥ ማድረግ ሕገ መንግስታዊ አይደለም። ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ የተቃውሞ ሰልፍ ላይ የተወሰኑ ገደቦችን ማስገባት ተፈቅዷል። አንዱ ገደብ፣ የተቃውሞ ሰልፉ የሚካሄድበት ቦታ ነው። ተቃውሞ ሰልፉ ሊዘጋ የሚችለው፣ የሁከት፣ የስርዓት አልበኝነት፣ የትራፊክ መስተጓጎል ወይም ሌሎች የሕዝብን ደኅንነት ቀጥተኛ ስጋት የምያስከትል ግልጽ የሆነ አደጋ በሚኖርበት ጊዜ ነው።

### የተቃውሞ ሰልፍ በኃይል ሊበተን የሚችለው መቼ ነው?

ፖሊስ ሰልፉ እንዲበተን ማዘዝ የሚችለው ሌላ አማራጭ ከሌለው ብቻ ነው። ተቃውሞ በሃይል በሚበተንበት ግዜ፣ ፖሊስ ጉልበትን፣ ከጎማ የተሰሩ ጥይቶችን፣ ሀሰተኛ ባሩድ የተሞላ ከረጢቶችን፣ ትክክለኛ ጥይቶች፣ ቲዘሮችን፣ አስለቃሽ ጭስን እና/ወይም/ በርበሬ የሚረጭን በጠቀም አካላዊ ጉዳት በማድረስ ይታወቃል። አደጋ በሚኖርበት ግዜ፣ ፖሊስ ተቃውሞን ለመበተን ኋይልን እንደ የመጨረሻ አማራጭ ሊጠቀም ይችላል።

## በተቃውሞ ሰልፍ ላይ ቪዲዮ መቅረጽ ወይም ፎቶግራፍ ማንሣት እችላለሁ?

በአደባባይ የሚታየውን ማንኛውንም ነገር መቅረጽ ወይም ፎቶግራፍ ማንሣት ሙሉ በሙሉ ሕጋዊ ነው። ይህ በሕግ አስከባሪዎች እና በተቃዋሚዎች የሚደረጉ ግንኙነቶችን መመዝገብን ያካትታል። የፖሊስ መኰንኖች ያለ ማዘዧ ፎቶግራፎችን ወይም ቪዲዮን ጨምሮ ስልክዎን ወይም ሌላ መሳሪያዎን መውሰድ ወይም ለማየት መጠየቅ አይችሉም።

## ተቃውሞ ማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው?

የተቃውሞ ሰልፍ አካላዊ እና ሕዝባዊ የሆነ የሲቪክ እንቅስቃሴ ነው። አንድን ጉዳይ ወይም ምክንያት ትኩረት እንዲሰጠው ሰውነትዎን እየተጠቀሙ ነው። አብዛኞቹ ተቃውሞዎች ሰላማዊ ቢሆኑም፣ በመንግሥት ወይም በሌሎች፣ ተቃውሞዎች ላይ የኃይል እርምጃ አጋጣሚዎች አሉ። አንድ ተቃውሞ አደገኛ እየሆነ ነው ብለው ካሰቡ ወይም የመበተን ትእዛዝ ከታወጀ፣ መተውን መምረጥ ይችላሉ።

## በመቃወም ላይ ሳለሁ ብታገትስ ወይም ብታሰርስ?

ለመረጋጋት ይሞክሩ። ለመሄድ ነጻ ነዎት ወይስ አደሉም የፖሊስ መኮንኑን ይጠይቁ። ነጻ ካልሆኑ፣ ጠበቃዎ እስከሚመጣ ድረስ በአምስተኛው ማሻሻያ (Fifth Amendment) መሰረት ዝም የማለት መብትዎ መጠቀም ይችላሉ። “በአምስተኛው ማሻሻያ መሰረት ዝም የማለት መብቴን እየተጠቀምኩ ነው እናም ጠበቃዬ እስከሚገኝ ድረስ አልናገርም” በሚል አዎንታዊ እና ግልጽ በሆነ መንገድ መግለፅዎን ያረጋግጡ። ንብረቶችዎን እንዲፈተሹ መስማማት የለብዎትም፤ ነገር ግን መሣሪያ አለው ወይም ወንጀል ፈጽመዋል ብለው ካሰቡ፣ አንድ የፖሊስ መኰንን “የሰውነት ፍተሻ” ሊያደርግ ይችላል። ዝም ማለት የተሻለ እንደሆነ ሁሉ፣ በተቻለ መጠን ፍተሻን እምቢ ማለት ሁልግዜ የተሻለ ነው። ታግተው ከሆነ ማንነትዎን መግለጽ አለብዎት። ሌሎች ጥያቄዎች ውድቅ ሊደረጉ ይችላሉ፤ ሕጋዊ ትዕዛዞች ግን ሁሉንም ይከተሉ። ከአንድ መኰንን የሚመጣውን ጥያቄ ነው ወይስ ትእዛዝ መለየት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

## በመቃወም ላይ ሳለሁ ብታገትስ ወይም ብታሰርስ?

መንግሥት በመላ አገሪቱ ተቃውሞዎችን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ተግባራዊ እያደረገ ነው። ይህ በስልክ በኩል የሚላኩ መረጃዎችን ለመጥለፍ የስቲንግሬይ ቴክኖሎጂን መጠቀምንም ያካትታል። ይህ ቴክኖሎጂ፣ የሬድዮ ሞገድ ማሰራጫ ወይም የዋይፋይ ሆትስፖት መስሎ ስልክዎትን በማታለል ከስልክዎ ጋር ተገናኝቶ፣ የምትልኩትን መረጃ ሁሉ ይመዘግባል። መንግሥት በተቃውሞ ወቅት የሞባይል ስልክ መሰናክሎችን በመጠቀም፣ ስልኮች ከሌሎች መሣሪያዎች ጋር የመገናኘት አቅማቸውን የሚያስተጓጉል መሆኑም ይታወቃል።

## መብቶችዎ የተጣሱ መስለው ከተሰማዎት፦

- ከቻሉ፣ የተከሰተውን ነገር በማስታወሻዎ ላይ ይጻፉ። የፖሊስ መኮንኖችን ባጅ እና የፖሊስ መኪና ታርጋ ቁጥሮች እንዲሁም የሚሠሩበትን ኤጀንሲ ለማካተት ይሞክሩ።
- የምስክሮችን የእውቂያ መረጃ/አድራሻ ይያዙ።
- ለደህንነትዎ የማያሰጋ ከሆነ፣ የክስተቱን ቪዲዮ/ፎቶግራፍ ቀርጸው ይያዙ።
- ምንም አይነት ጉዳትን ፎቶግራፍ አንሱ፤ አስፈላጊ ከሆነ፣ የህክምና እርዳታ ይጠይቁ።

**መብቶችዎን ይወቁ ተጨማሪ መመሪያዎችን ማግኘት ይችላሉ፣ ስልጠና መጠየቅ ይችላሉ፣ እና ተጨማሪ በ**

**aclunv.org.**

